

## የሙርናሉንግ ፓርክ መክፈቻ በዓልን ያክብሩ

**በፍሌሚንግተን ግቢ እምብርት ውስጥ በሚገኘው በአዲሱ የሙርናሉንግ ፓርክ ውስጥ ሁሉም ሰው የሚደሰትበት ነገር አለ።**

ፓርኩ በዉሩንጄሪ ዎይ ዉሩንግ ሽማግሌዎች 'ሙርናሉንግ' የሚል ስያሜ ተሰጥቶታል፣ ትርጉሙም 'ንብ' ማለት ነው። እና የእንቅስቃሴ ቀፎ ይሆናል።

ለልጆች የመጫወቻ ሜዳዎች እና የተፈጥሮ መጫወቻ ቦታዎች እንዲሁም በሳር የተሸፈኑ የሽርሽር ቦታዎች አሉ። ከቤት ውጭ የአካል ብቃት እንቅስቃሴ መሳሪያዎች፣ የብስክሌት እና የእግር ጉዞ መንገዶች እና የመቀመጫ ቦታዎችም አሉ።

ሞቅ ያለ የዊንተር ፓርክ ዝግጅት ማድረግ የፍሌሚንግተን ግቢን እንደገና በምናድስበት ጊዜ ላሳዩት ትዕግስት እና ስለተረዱን የአካባቢውን ማህበረሰብ የምናመሰግንበት መንገድ ነው።

በሚቀጥሉት ሳምንታት በግቢው ዙሪያ ባሉ ፖስተሮች እና በድረ-ገጻችን ላይ የዝግጅቱ ዝርዝር መረጃ ስለምናካፍል በትኩረት ይከታተሉ።

### ይምጡ እና ከትምህርት በኋላ በሚኖረው ሞቅ ያለ የዊንተር ፓርክ ዝግጅት ይቀላቀሉን

**ሐሙስ፣ ኦገስት 6 ከ3.30–5.30 ሰዓት(pm) ከቀትር በኋላ**



- ትኩስ ምግብ እና መጠጦች
- የልጆች ጨዋታዎች እና መዝናኛዎች

### እንደተገናኙ መቆየት


ተሳታፊ ለመሆን ከታች ያለውን ይጎብኙ፦

የምክክር አስተያየት

ወቅታዊ መረጃ ለማግኘት ይመዝገቡ

ተሳታፊ  ሆኖ ለመቆየት ከታች ያለውን ይጎብኙ፦

homes.vic.gov.au/flemington-precinct



በማህበራዊ ሚዲያዎች ላይ **Homes Victoria** ብለው በመፈለግ ይከተሉን።

በቪክቶሪያ መንግስት የተፈቀደ እና የታተመ ፣ Treasury Place, Melbourne። © የቪክቶሪያ ግዛት፣ ሆምስ ቪክቶሪያ፣ ጁላይ 2026። (HV020726)። በFinsbury Green, Melbourne Victoria, 3000 የታተመ።

More Homes For Victorians | VICTORIA State Government

Amharic | አማርኛ

ጁላይ / ኦገስት 2026

homes victoria

BIG HOUSING BUILD

# ፍሌሚንግተን

የማህበረሰብ ወቅታዊ መረጃ



### በአዲሱ የሙርናሉንግ ፓርክ ሞቅ ያለ የዊንተር ፓርክ ዝግጅት

ይምጡ እና አዝናኝ እና ለቤተሰብ ተስማሚ በሆኑ እንቅስቃሴዎች ይደሰቱ። የዝግጅቱ ዝርዝር መረጃ ገጽ 4 ላይ ይገኛል።

### ፍሌሚንግተንን በቀለም እና መናፈሻዎች ማስዋብ

በሆላንድ ኮርት ልማት ላይ የግድግዳ ሥዕል እና በአዲስ ትንሽ መናፈሻ ላይ ይሰራል።


### የነዋሪዎች መረጃ ክፍለ ጊዜዎች ቀጥለዋል

የቅርብ ጊዜ ስብሰባዎች በነዋሪዎች ዘንድ ጥሩ ተቀባይነት አግኝተዋል። እንዲቀጥሉ እናደርጋቸዋለን፣ ለዝርዝር መረጃ የበራሪ ወረቀት ፎየር ፖስተሮችን ይመልከቱ።

ቤቶች ቪክቶሪያ የአቦርጂናል እና የቶረስ ስትሬት ደሴት ነዋሪዎችን የምድሪቱ ባህላዊ ጠባቂዎች አድርገው ይቀበላሉ እና ያለፉትን እና የአሁኑን ሽማግሌዎቻቸውን እውቅና ሰጥተዋል እና ያከብራሉ።

# በፍሌምንግተን ውስጥ ምን እየሆነ ነው

ጁላይ / ኦገስት 2026




**ሆላንድ ኮርት (Holland Court)**
286 አዳዲስ ቤቶች እና የህዝብ መናፈሻ ፓርኮች

**አዲስ ትንሽ ፓርክ**
ስራ በሂደት ላይ ነው።

**126 እና 130 ሬስኮርስ ሮድ (Racecourse Road)**

**የኤሌክትሪክ ስራዎች**

- በቅድመ ማስጠንቀቂያ ስርዓቶች ላይ የኤሌክትሪክ ስራዎች ቀጥለዋል

**የቆሻሻ መሰብሰብ፣ ጥገና እና የአደጋ ጊዜ አገልግሎቶች ተደራሽነት በማንኛውም ጊዜ ይጠበቃል።**

**120 ሬስኮርስ ሮድ (Racecourse Road)**

ሕንጻው ደህንነቱ የተጠበቀ ነው

**የጣቢያ መሠረተ ልማት ስራዎች**

ለወደፊት የኤሌክትሪክ እና የውሃ ግንኙነቶችን አስተማማኝ እንዲሆኑ እያረጋገጥን ነው። የሚከተሉትን ሊያስተውሉ ይችላሉ፦

- የመሠርሠር፣ የቁፋሮ እና የመጋዝ መሳሪያዎች እና ከባድ ተሽከርካሪዎች
- አንዳንድ ዛፎችን እና እፅዋትን ማስወገድ
- የላይኛው መብራትን ማዛወር
- በመኪና ማቆሚያ እና በእግረኛ መንገዶች ላይ ለውጦች

**12 ሆላንድ ኮርት (Holland Court)**

ሕንጻው ደህንነቱ የተጠበቀ ነው

**ቁልፍ**

- የመኪና ማቆሚያ ተዘግቷል
- የመኪና ማቆሚያ ክፍት ነው
- የአካል ጉዳተኛ የመኪና ማቆሚያ
- የ 5 ደቂቃ መውረጃ
- የአምቡላንስ ማቆሚያ
- የትራፊክ መዳረሻ
- የእግረኞች መዳረሻ
- የታጠረ የስራ ዞን

## በአካባቢዎ በሚሰሩ ስራዎች ዙሪያ ደህንነትን መጠበቅ

የደረጃዎችን ደህንነት ለመጠበቅ እንደ ጫጫታ፣ አቧራ እና ንዝረት ያሉ ነገሮችን በመደበኛነት እንቆጣጠራለን።

### በአከባቢው መዛወር

- ሥራ ከመጀመሩ በፊት አጥር ሁል ጊዜ በቦታው ላይ ይደረጋል
- ተጨማሪ የጭነት መኪናዎችን መቼ እና የት እንደሚጠብቁ እንነግርዎታለን
- በእግረኛ መንገዶች ወይም መንገዶች ላይ በሚደረጉ ለውጦች ዙሪያ ደህንነቱ በተጠበቀ ሁኔታ ለመንቀሳቀስ ሁል ጊዜ ምልክቶችን ይከተሉ
- እርስዎን ለመርዳት እዚያ ሲሆኑ የትራፊክ አስተዳደር ሰራተኞች መመሪያዎችን ይከተሉ

### ቁሳቁሶችን ደህንነቱ በተጠበቀ ሁኔታ ማስተዳደር

- አደገኛ ቁሳቁሶችን ለማስወገድ እና ለማጽዳት ጥብቅ የደህንነት ደረጃዎች ሁል ጊዜ ይዘጋጃሉ
- አደገኛ ቁሶች ያሉባቸውን ቦታዎች ማስወገድ እንዲችሉ ምልክቶች ሁል ጊዜ ይኖራሉ
- ሰራተኞች መከላከያ ልብስ ለብሰው ሊመለከቱ ይችላሉ

### መዳረሻን ማቆየት

- የአደጋ ጊዜ አገልግሎት ተደራሽ እንዲሆን በማንኛውም ጊዜ ይጠበቃል
- የአካል ጉዳተኞችን የመኪና ማቆሚያ ጨምሮ ደህንነቱ የተጠበቀ የመኪና ማቆሚያ መዳረሻ መገኘቱን ይቀጥላል
- ለጊዜያዊ የእግረኛ መንገዶች መብራት ሁል ጊዜ ይደረጋል

ስራችን የሚመራው በምክር ቤትዎ መደበኛ የስራ ሰዓት ነው፦

**ከሰኞ እስከ አርብ**
ከ 7am እስከ 6pm

**ቅዳሜ**
ከጠዋቱ 9 ሰዓት
እስከ ምሽቱ 3 ሰዓት

አንዳንድ ጊዜ ከእነዚህ ሰአታት ውጭ ለመስራት የምክር ቤት ፈቃድ ያስፈልጋል ነገርግን ይህ ከተከሰተ ነዋሪዎችን እናሳውቃለን።

ሁሉም ስራዎች የሚከናወኑት በከፍተኛ የደህንነት ደረጃዎች እና የህግ መስፈርቶች ነው።

**ስለ ስራው ወቅታዊ መረጃዎች ለማግኘት የፎየር ማስታወቂያ ሰሌዳዎችን ይመልከቱ።**

ተጨማሪ መረጃ የሚፈልጉ ነዋሪዎች የአካባቢዎን የቤቶች ቢሮ ያነጋግሩ፦

**1300 360 462**

**ascotvale.housing@dffh.vic.gov.au**

በቋንቋዎ ውስጥ መረጃን ጨምሮ ተጨማሪ መረጃ ለማግኘት የሚከተሉትን ይጎብኙ - **homes.vic.gov.au/information-in-your-language**

ለአጠቃላይ ጥያቄዎች የኢሜይል ኣድራሻ:

**enquiries@homes.vic.gov.au**